# የሞት ዕኩልነት

እግዜር በፈጠረው- ሰማይና ምድር
ተራራ ሽንተረር- ውቅያኖስ ባህር
ያገባኛል ብሎ- ሰው ባለቤት ሆኖ- ድንበር አበጅቶ
የከርሰ-ምድር ሐብት- በስፋት አካብቶ
አንተ ከዚያ ወዲህ- አንች ከዚህ ወዲያ- ብሎ ተከፋፍሎ
አንዱን እጅግ ደልቶት- ሌላው ተበድሎ
ይኖራል ይሞታል- የመኖር- ሕግ ሆኖ።

አንዱ ባለፀጋ- የተትረፈረፈው
ሌላው ምስኪን ደሃ-ይበላው ይጠጣው-
ይለብሰው የሌለው
የዓለም መልክ ሆነና- ህይወት ቸንጉርጉሩ
የሰው ልጅ ይኖራል- ገንዘብ ሆኖ ነውሩ
ንብረት በለጠና- ከሰብዓዊ ክብሩ።

ሠራዊት መንግስታት- አቤት ብለውለት
ሐብታሙ ይኖራል- ዓለም አድልታለት
ከውሻ አንሶ ደሃው- ማጣቱ ወንጅሎት
እሱም ኖረ ተብሏል- ዓለም አድማበት
የሰው ልጅ ሕሊና- እንዲህ ተመሳቅሎ
ፀጋን አመሥግኖ
ድህነት ኮንኖ
ለኃይል አቤት ብሎ
ደካማውን ገድሎ
ህይወት ነው ይለናል- "መኖር" ስሙ ሆኖ።

ልክ እንደ እግዜር ሆኖ- ሰው ቢሰራውማ- ሰማይና ምድሩ
ደሃና ደካማ ባልኖሩበት ነበር- ገና ከጅምሩ
ጉልበታም ለብቻው - ልክ እንደሂትለር
ሞልቶ ከተረፈው- ከባለፀጋው ጋር



EthioLion.Com

እኛ ብቻ እንኑር- ብሎ ባለን ነበር
ዳሩ አምላክ ሆነና- የዚህ ዓለም ንጉስ
ደሃውም ሃብታሙም-
ደካማና ኃይለኛ እኩል ባይወደስ
የሞት ቀን ሲመጣ- ሰው ሲመለስ ከአፈር
ዕኩል መሆናቸው- ያኔ ነው የማይቀር።

እናም ሂሳብ ሳስብ- አንድና አንድ ደምሬ
ዕልፍ አዕላፍ ብደርስ- ከአሃዱ ጀምሬ
አራት ነጥብ ሳደርግ- ስንኝ ቋጥሬ
መደምደሚያው ሆነ- የድምር ውጤቱ
ዕኩል የሚሆነው- ሰው በሰውነቱ
ሲሞት ብቻ ሆኖ- አፈርኩ በስሌቱ
በአንድዬ እምላለሁ- ቀፈፈኝ እውነቱ።

ዳግማዊ ዳዊት
ሰኔ 2002 ዓ.ም.
Ethio_dagmawi@yahoo.com



EthioLion.Com
Ethiopia will prevail !